# በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

## የአካባቢ፣ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን

## የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ የ1ኛ ሩብ ዓመት ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት

ጥቅምት /2014 ዓ.ም

አዲስ አበባ

**ማውጫ**

<u>ርዕስ</u> ገፅ

Executive Summaryድርሞ) --------------------------------------------------------------------- 2

**መግቢያ** ---------------------------------------------------------------------------------------------------- 5

**ራዕይ ፣ ተልዕኮ እና እሴቶች**----------------------------------------------------------------------------- 6

1. ክፍል አንድ------------------------------------------------------------------------------------- 7
   1.1. የ2014 በጀት ዓመት የመጀመሪያው ሩብ ዓመት በቁልፍ የውጤቶች ሳይ የተመሰረተ የፊዚካል ዕቅድ አፈፃፀም --------------------------------------------------------------------------- 7
2. ክፍል ሁለት ------------------------------------------------------------------------------------ 22
   2.1. የተቋሙ የፋይናንስ ፐሮግራም በጀት አፈጻጸም ---------------------------------------------- 22
   2.2. የኦዲት ግኝት ምልከታ ------------------------------------------------------------------- 22
   2.3. የለውጥና የአገልግሎት አሰጣጥ አፈፃፀም------------------------------------------------- 22
   2.4. ለክልሎች የተሰጠ አቅም ግንባታ ------------------------------------------------------ 23
3. ክፍል ሶስት ፡- በአፈፃፀም ሂደት ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች ---- 23
   3.1. ተግዳሮቶች ---------------------------------------------------------------------------- 23
   3.2. የተወሰዱ/ሲወሰዱ የሚገባቸው የመፍትሔ እርምጃዎች ----------------------------------- 23
4. በየዘርፉ ቁልፍ የውጤት መስኮችንና ቁልፍ የውጤት አመልካቾችን(የፖሲሲ ማትሪክሱን) መሰረት በማድረግ የሚዘጋጅ ------------------------------------------------------------------------24

## ድርሞ /Executive Summary/

የተቋሙ የ2014 በጀት ዓመት እቅድ ከተቋሙ የቀጣይ 10 ዓመት መሪ እቅድ በመመንዘርና አሳታፊ በሆነ መልኩ በማዘጋጀት የታቀዱ ግብ ተኮር ተግባራት ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት በዕቅዱ መሰረት እንዲተገበሩ ተደርጓል፡፡

የደን ሀብት በርካታ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና አካባቢያዊ ጥቅሞችንና ግልጋሎቶችን የሚያበረክት ሀብት ይሁን እንጂ በሀገራችን በደን ሀብት መመናመን ምክንያት በርካታ ችግሮች ተከስተው ይስተዋላሉ፡፡ እነዚህንም ችግሮች ለመቅረፍ የ2013 በጀት ዓመት የሥራ ተግበራ ወቅት በጥንካሬና በእጥረት እንዲሁም የ10 ዓመት መሪ ዕቅድ መነሻ በማድረግ የ2014 ዓ.ም ዕቅድ እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡ በሩብ ዓመቱ ከሮያሊቲ እና ከተወረሱ የደን ምርት ውጤቶች ሽያጭ 54.408606 ሚልዮን ብር ማሰባሰብ ተችሏል፡፡ ለ125,786 (ሴ 29,285) ለሚሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎች በህግ ተከባሪነት ዙሪያ የግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ ተሰርቷል፡፡ **3.26 ቢሊዮን** የደን ችግኞች **በ699,231.05 ሄ/ር** ላይ ተከላ ማካሄድ ተችሏል፡፡ ከዚህ ውስጥ **በ67,578.9** ሄ/ር ላይ የተተከለው **42,111,161** የቀርከሀ ችግኝ ነው፡፡

የ2020ና 2021 ሃገራዊ የደን ሽፈን መጠንን ለማስላት የሚያስችሉ 12,926 ወካይ ናሙናዎችን መሰብሰብ ተችሏል፡፡ 19.47 ሚሊዮን ሄ/ር ነባር የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ደኖችን ለመጠበቅ፣ ለመንከባከብና በዘላቂነት ለመጠቀም የሚያስል ክትትልና ድጋፍ ተደርጓል፡፡ በ2.12 ሚ/ን ሄ/ር የተፈጥሮ ደኖችን በአሳታፊ የደን አስተዳደር ስርዓትን በመተግበር በዘላቂነት እንዲጠበቁና ተገቢውን ግልጋሎት እንዲሰጡ ለመማድረግ ተችሏል፡ ፡ 38,374(ሴት 13038 ) ለሚሆኑ ለወጣቶችና ሴቶች በዘርፉ ጊዜያዊ እና ቋሚ ስራ ዕድል እንዲፈጣርላቸው ተደርጓል፡፡ 303.7 ቶን የደን ምርት ውጤት ወደ ውጭ ሀገር በመላክ 0.114 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር የውጭ ምንዛሬ (5.127606 ብር) ለማግኘት ተችሏል፡፡ በፌዴራል ደረጃ ከተለያዩ ክልሎች ለተወጣጡ ለ300 ልማት ጣቢያ ባለሙያዎች በመሰረታዊ የደን ልማትና ጥበቃ ዙሪያ በሆለታ ግ/ቴ/ሙ/መ/ኮሌጅ እና በመርሎስመርያም ግ/ቴ/ሙ/መ/ኮሌጅ በያንደንዱ ለአንድ ወር ስልጠና እንዲሰ ተደርጓል፡፡ ለ40 (ሴት 4) የክልልና ፌደራል ባለሙያዎች ስልጠና እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡ ለ280 ባለሙያዎችንና የተለያዩ ባለድርሻ አካለት በዘርፉ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ ተሰርቷል፡፡ በክልሎች ደረጃ ከክልል እስከ ቀበሌ በተከሄደዉ ወርክሾና ስልጠና ላይ ለ2,648(ሴት 1,064) ባለድርሻ አካላትን ማሳተፍ ተችሏል፡፡

የክትትል እና ቁጥጥር ስራን ለመስራት ታቅዶ በስድስቱም አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ላይ የክትትል እና ቁጥጥር ስራ የተሰራ ሲሆን በሶስቱ አግልግሎት ሰጪ ተቋማት (ፒራሚድ ሪዞርት፣ አዱላላ ሪዞርት እና ባቡጋያ ሪዞርት) በ2013 ዓ.ም ክትትል ተደርጎ ደካማ የአካባቢ አያያዝ የነበራቸዉ እና ማስጠንቀቂያ የተሰጣቸዉ

ሲሆኑ ሶስቱ ተቋማት ማለትም ሃይሌ ሪዞርት፣ ጀ ሪዞረት እና አዳማ አጠቃላይ ሆስፒታል ለመጀመሪያ ጊዜ የታዩ ተቋማት ናቸዉ፡፡ በአብዛኛወቹ ክትትል የተደረገባቸዉ ሪዞርቶች የደረቅ ቆሻሻ እና የፍሳሽ ቆሻሻ ልየታና ቅነሳ ሳይንሳዊ የሆኑ የአያያዝ እና የአስተዳደር ከዚህ በፊት ያልነበራቸዉ ሲሆን በተሰጠታቸዉ ግብረ መልስ መሰረት አዱሳሳ ሪዞርት እና ፒራሚድ ሪዞረት የነበረዉን ችግር አስተካለዉ የተሻለ የቆሻሻ አያያዝ ስርአት ዘርግተዋል፡፡

በአምስት የማምረቻ ተቋማት ላይ ክትትል እና ቁጥጥር ለማድረግ ታቅዶ በኦሮሚያ ክልል ሶስት (አቢሲንያ ብረታ ብረት ፋብሪካ ፣ሀበሻ steel mills plc እና አዳማ ቆርቆሮ ፋብሪካ) እንዲሁም በሲዳማ ክልል ሁለት በድምሩ አምስት የማምረቻ ተቋማት ላይ ቁጥጥርና ክትትል ስራ ተሰርቷል፡፡ በዚህም ለአቢሲንያ ብረታብረት ፋብሪካ እና ሀበሻ steel mills plc ፋብሪካዎች የመጨረሻ ማስጠንቀቅያ ለመስጠት ዘገባው እየተጠናቀረ ይገኛል፡፡ እንዲሁም በአዳማ ቆርቆሮ ፋብሪካ ፣ ቢ ጂ አይ ቢራ ፋብሪካ እና የሀዋሳ ሚሲንየም ፔፕስ ፋብሪካዎች ሳይ ግብ-ረመልስ ለመስጠት በሂደት ላይ ነው፡፡

በ2014 በጀት ዓመት 1ኛው ሩብ ዓመት በአየር ንብረት ለውጥ እና ብዝሀ ህይወት ጄነራል ዳይሬክቶሬት በዋናነት በዘርፍ መ/ቤቶች የክትትልና ድጋፍ በማድረግ እዲሁም አስፈላጊውን ግብረ መልስ በመስጠት ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ስልት በ2014 ዓመታዊ እቅዳቸው ውስጥ 100% አካተው ማቀዳቸውን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በበጀት ዓመቱ ለሚካሄዱ የአካባቢ ስምምነቶች የድርድር መድረኮች በተለይም 26ኛው የተ.መ. የአየር ንብረት ለውጥ ጉባኤ (ኮፕ 26) ተያያዥ የሆኑ 3 መድረኮች መሳተፍ የተቻለ ሲሆን ለእነዚህና ለሌሎች ለመድረኮች የሚሆኑ 6 የሀገራችንን ፍላጎትና አቋም የሚያሳዩ ሰነዶችን ማዘጋጀት ተችሏል፡፡ እንዲሁም ለአካባቢ ስምምነቶች ትግበራ የሚሆን 9 አጋርነቶችን የመፍጠር/ የማጠናከር የክትትልና ድጋፍ ስራየተሰራ ስሆን በአከባቢ ስርዓተ-ምህዳር ግልጋሎት ዋጋ ትመና በኩል በ2013 በጀት ዓመት የተጀመሩ የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት የሚያመነጩትን ዋጋ ትመና ጥናት ሰነዶችን 50 በመቶ ተጠናቋል፡፡

የድጋፍ ሰጪ ዘርፍ አገልግሎት አሰጣጥን በማሻሻል ውጤታማ በማድረግ ዜጎች በህገ መንግስቱ የተጎናፀፉትን በንጽህና ጤናማ አካባቢ የመኖር መብትን ለማረጋገጥ የዘርፉን የማስፈጸምና የመፈጸም አቅም ለማሳደግ ለ600 ፈጻሚና አስፈጻሚ አካላት ስልጠና መስጠት ታቅዶ 75181 ፈፃሚና አስፈፃሚ አካላት ስልጠና ተሰጠቶዋል፡፡

በአካባቢ፣ ደንና አየር ንብረት ለውጥ ህጎች፣ መብቶች፣ ግዴታዎችና ስትራተጂዎች ላይ በሩብ ዓመት 0.5 ሚሊዮን በየደረጃው ለሚገኙ የባለድርሻ አካላትና ለተለያዩ አደረጃጀቶችና የህብረተሰብ ክፍሎች ግንዛቤን

በማሳደግ፣ ተሳትፎን ማጎልበትና መረጃን ተደራሽ ለማድረግ ታቅዶ ለ1.5 ሚሊዮን ህብረተሰብ ግንዛቤ ተፈጥሯል፡፡

በዘመናዊ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ በመጠቀም የዘርፉን የመረጃ አሰባሰብ፣ አያያዝናአጠቃቀም እና የልውውጥ ስርዓት ለማዘመን 1 ስረዓት ለመዘርጋ ታቅዶ አንድ የዛፍ ዘር ገበያ ትስስርና ክትትል መረጃ ስረዓት ተዘርግቷል፡፡

በአካባቢ፣ ደንና አየር ንብረት ለውጥ የሚተገበሩ ፕሮግራሞችና፣ ፕሮጀክቶች ለ62,500 ሴቶችና ወጣቶች የስራ ዕድል በመፍጠር ተጠቃሚነታቸውን ለማረጋገጥ ታቅዶ 7,773 ለሴት፣ እና ለ12,958 ወንድ በድምሩ ለ20,731 ሴቶችና ወጣቶች ስራ እድል ለመፍጠር ተችሏል፡፡

ለዘርፉ በ2014 በጀት ዓመት ከተመደበው 46,812.283 ብር የመደበኛ በጀት በዚህ ሩብ ዓመት 29,642,790.7 ተቅዶ 27,512,285.36 ስራ ሳይ እንድውል ተደርጓል፡፡ እንዲሁም ለመ/ቤታን ከተመደበው 206,871,534.00 ብር በዚህ ሩብ ዓመት 33,062,103.58 ጥቅም ሳይ ማዋል ተችሏል፡፡

ሰራተኞች የረጅም ጊዜ የትምህርት ዕድልተጠቃሚ እንድሆኑ በአገር ውስጥ 7 በውጭ አገር 8 ሰራተኞች በድምሩ 15 ሰራተኞች የረጅም ጊዜ ትምህርት ተጠቃሚ ተደርጓል፡፡

**መግቢያ**

የአካባቢ፣ የደንና የአየር ንብረት ለዉጥ ኮሚሽን የቀጣይ አስር ዓመት መሪ የልማት ዕቅድ ያለፉት ዓመታት አፈጻጸም በመገምገም ለቀጣይ አስር ዓመት የሚደረስባቸዉን ግቦች ከሀገራዊ የልማት እድገት የትኩረት አቅጣጫዎች፣ ከዘላቂ የልማት ግቦች፣ ከአፍሪካ አጀንዳ 2063፣ ሀገራችን የፈረመቻቸዉ አለም አቀፍ የአካባቢ ስምምነቶች የትግበራ ደረጃ እንዲሁም ከዘርፉ አለም አቀፍ፣ አህጉራዊና ሀገራዊ ነባራዊ ሁኔታዎች ጋር በማስተሳሰርና በማጣጣም ያዘጋጀ መሆኑ ይታወቃል፡፡ይህን መሪ እቅድ እና የ2013 በጀት አፈፃፀም ግምገማን መነሻ በማድረግ የ2014 በጀት አመት እቅድን በዝግጅት ምዕራፍ ሁሉንም ባለድርሻ አካላትን ባሳተፈ መልኩ ተዘጋጅቶ ግብአቶችን በማሟሳት እና ፈጻሚን ለስራ ዝግጁ በማድረግ ወደ ተግባር ተገብቷል፡፡

በበጀት ዓመቱ የታቀዱትን ሥራዎች ለማሳካት በዝግጅት ምዕራፍ ያለፈውን በጀት ዓመት ማጠቃለያ ግምገማን በማድረግ የሪፎርምና መልካም አስተዳደር ችግሮች እና የኪራይ ሰብሳቢነት ምንጮች የመለየትና የጋራ የማድረግ እንዲሁም በዋና ዋና ግቦችና አበይት ተግባራት ላይ ከባለድርሻ አካላት ጋር የጋራ አቅጣጫ እንዲያዝ ተደርጓል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ በትግበራ ምዕራፍ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ (ለአ/ን/ለ/የማ/አ/ኢ) በሚመለከታቸዉ ሴክተሮች ሜይንስትሪም መደረጉን የማረጋገጥ ፣ ለአ/ን/ለ/የማ/አ/ኢ ግንባታ የሚውል የፋይናንስ ሀብት ከገንዘብ ሚኒስቴር ጋር በጋራ የማፈላለግ ፣ የአየር ንብረት ለውጥ ድርድርን ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችሉ ቅድመ ዝግጅቶችን የማድረግ ፣ የአካባቢ ህግ ተከባሪነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ድጋፍ ፣ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ እንዲሁም ብክለት በሚያስከትሉ ተቋማት ላይ አስተዳደራዊ እርምጃ የመውሰድ ፣ የተለያዩ ሚዲያዎችን በመጠቀም የህብረተሰቡን ለአ/ን/ለ/የማ/አ/ኢ ግንባታ ያለውን ግንዛቤና ተሳትፎ የማስፋት ፣ አካባቢያዊና ማህበራዊ ደህንነትን የሚያረጋግጡ ፈቃዶች የመስጠት ፣ የደን ዘርፉ ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ የሚያደርገውን አስተዋፅኦ ከፍ ለማድረግ የሚያስችል የልማትና ጥበቃ ስራዎችን በመስራት ድጋፍና ክትትል የማድረግ ፣ የደን ሽፋኑ እንዲያድግ እንዲሁም የደን ጭፍጨፋን ለመቀነስ የሚያስችሉ ሥራዎች በተያዘው በጀት አመት በዚህ 1ኛ ሩብ ዓመት ውስጥ የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት ናቸው

በአጠቃላይ 1ኛ ሩብ ዓመት (ከሐምሌ እስከ መስከረም 30/2014 ዓ.ም) ድረስ ያለው ዕቅድ አፈፃፀም፣ ከክልሎችና ከዘርፎች በቅንጅት የተከናወኑ ሥራዎችን እንዲሁም የድጋፍና ክትትል ሥራዎች፣ ያጋጠሙ ተግዳሮቶችና የተወሰዱ የመፍትሄ አቅጣጫዎችን የሚያሳይ ሪፖርት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

**የአካባቢ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን ራዕይ፣ ተልዕኮና እና ዕሴቶች**

**ራዕይ**

ዘላቂ የአከባቢና የደን አያያዝ ፣ ልማትና አጠቃቀምን በማረጋገጥ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚን በመገንባት ኢትዮጵያ በ2030 የአፍሪካ የብልጽግና ተምሳሌት ሀገር ሆና ማየት፣

**ተልዕኮ**

ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚን ለመገንባት የሚያስችሉ የአካባቢና የደን ሃብት አያያዝ፣ ልማትና አጠቃቀም ለዘላቂ ልማትና ለድህነት ቅነሣ አስተዋጽኦ እንዲያደርግ ሥርዓትን ማዘጋጀትና ተፈፃሚነቱን ማረጋገጥ ፣ ምርምርና የአረንጓዴ ቴክኖሎጂ ሽግግርን ማስተባበርና ማካሄድ ፣ ትምህርትና ግንዛቤን ማስፋፋት ፣ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ልማት ትግበራን በዘርፍ መ/ቤቶችና በክልሎች ማስተባበር ፣ የተግባሪዎችን አቅም መገንባት ፣ የደን ኢንቬስትመንትንና ግብይትን ማስፋፋት ፣ ዓለም አቀፋዊ የአካባቢና የአየር ንብረት ድርድሮችንና ስምምነቶች ትግበራን የመምራትና የመከታተል እና ወቅታዊ የአካባቢና እና የደን ሁኔታና ለውጥ ዘገባን ማዘጋጀት እንዲሁም የተጠሪ ተቋማትን ዉጤታማነት ማረጋገጥ ነው፡፡

**ዕሴቶች**

- የዜጎችን እርካታ ማረጋገጥ
- ከባለድርሻዎች ጋር በህብረት መስራት
- ለበጎ ለውጥ ዝግጁ መሆን
- የህግ የበላይነትን ማክበር
- የተልእኮ ቁርጠኝነት

# ክፍል አንድ

## የ2014 በጀት ዓመት የመጀመሪያው ሩብ ዓመት በቁልፍ የውጤቶች ላይ የተመሰረተ የፊዚካል ዕቅድ አፈፃፀም

**ግብ 1 ፡- የተገልጋዮች እርካታን ማሳደግ**

- በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት ቀልጣፋና ጥራት ያለው አገልግሎት በመስጠት የተገልጋይ እርካታ ለማሳደግ እንዲያስችል የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ ላይ ለፈጻሚውና በየደረጃው ላሉ አስፈጻሚ አካላት ግንዛቤ የመስጠትና ለፈጻሚው ተደራሽ የማድረግ ስራ ተሰርቷል፡፡

**ግብ 2 ፡- የሀብት አጠቃቀም ዉጤታማነትን ማሳደግ**

- በበጀት ዓመቱ ለኮሚሽን መ/ቤቱ ከተመደበው ብር 206,871,534.00 ውስጥ በመጀመሪያው ሩብ ዓመት ብር 33,062,103.58ደ ጥቅም ላይ ማዋል ተችሏል፡፡

**ግብ 3 ፡- የሀብት ግኝትን ማሳደግ**

- ከሮያሊቲ እና ከተወረሱ የደን ምርት ውጤቶች ሽያጭ በሩብ ዓመቱ 10 ሚልዮን ብር ገቢ ለመሰብሰብ **ታቅዶ** ከአማራ ክልል 30.2 ሚሊዮን ብር፤ ከኦሮሚያ ክልል 11.03 ሚሊዮን ብር፤ በደቡብ ክልል 5.956 ሚሊዮን ብር፤ እንዲሁም በሲዳማ ክልል 2.095 ሚሊዮን በድምሩ 49.281 ሚልዮን ብር መሰብሰብ ተችሏል፡፡

**ግብ 4. ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ትግበራን ውጤታማነት ማሻሻል፣**

**የቁልፍ ውጤቶች አፈፃፀም፡-**

- ለአየር ንብረት የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታን በ12 የዘርፍ መ/ቤቶች 100% ሜይንስትሪም መደረጉንና መተግበሩን ለማረጋገጥ ታቅዶ የዘርፍ መ/ቤቶች በዕቅዶቻቸው በCRGE በጋይድላይንና በሀገራዊ ማጣጣሚያ እቅድ በተቀመጠው አማራጮች መሰረት አካተው ማቀዳቸውን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡
- በሀገራዊ የማጣጣሚያ ዕቅዱ ላይ የተለዩትን 18 የማጣጣሚያ ዘዴዎች አካተው ተግባራዊ ያደረጉ ፕሮጀክቶች ድርሻ 35% ለማድረስ ታቅዶ Initiative for Effective Adaptation Resilient (IFE-AR) ፕሮጀክት ወደ ተግባር ለማስገባት አንድ ወረዳ በመምረጥ ከወረዳ አመራሮች፣

ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት፣ እና ከዘርፍ የተወከሉ ፎካሎች ጋር የጋራ ውይይት በማድረግ የወረዳው የ10 ዓመት ረቂቅ ዕቅድ ተዘጋጅቷል፡፡

- የሀገራዊ የማጣጣሚያ እቅድ የትግበራ ዝግጅት (NAP-Readiness Project) ፕሮጀክት የማስጀመሪያ ዎርክሾፕ ከGGGI ጋር በመተባበር የተዘጋጀ ሲሆን በቀጣይ የሚሰሩ ስራዎች ከፌደራል፣ ከክልልና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመወያየት የድርጊት መርሃ ግብር ተዘጋጅቶ እንዲሁም ፎካል ፖይንቶች እንዲመደቡ በማድረግ ሥራው ተጀምሯል፡፡

ዋና ተግባር 2፡- **አየር ንብረት የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታ ትግበራ የሚረዱ ሰነዶችን መዘጋጀት**

የቁልፍ ውጤቶች አፈፃፀም፡-

ለአየር ንብረት የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታ ትግበራ የሚረዱ 2 ሰነዶችን ለማዘጋጀት ታቅዶ 2 ሰነዶች ተዘጋጅተዋል፡፡

- Long Term - Low Emission Development Strategy በፓሪሱ የአየር ንብረት ለውጥ ስምምነት መሰረት ለማዘጋጀት የማስጀመሪያ ዎርክሾፕ ከGGGI ጋር በመተባበር በማዘጋጀት በቀጣይ የሚሰሩ ስራዎች ተለይተው በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ቡድን በማደራጀት ሥራው ተጀምሯል፡፡
- ለአየር ንብረት የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታን ለመተግር የሚረዳ የግብርናና የደን የአቅም ግንባታ ክፍተት ለመለየትና የድርጊት መርሃ ግብር ለማዘጋጀት ረቂቅ የዳሰሳ ጥናት ሰነድ ተዘጋጅቷል፡፡

## ዋና ተግባር 3 ለአረንጓዴ ልማት ትግበራ ውጤታማነት አጋዥ የሚሆኑ 21 የአረንጓዴ ቴክኖሎጂዎችን እንዲተገበሩ ማድረግ

የቁልፍ ውጤቶች አፈፃፀም፡-

- የተለዩና የተዋወቁ የአረንጓዴ ቴክኖሎጅዎችን ዘርፎችና ክልሎች በዕቅዶቻቸው ውስጥ አካተው እንዲተገብሯቸው አንድ ጊዜ የክትትልና ድጋፍ ስራ ለማከናወን ታቅዶ አንድ ጊዜ ተከናውኗል፣

- ከተለዩና ከተዋወቁ አገር በቀል የአረንጓዴ ቴክኖሎጂዎች ውስጥ ወደ ከባቢ አየር የሚለቀቁ በካይ ጋዞችን የሚያስቀር ቴክኖሎጂ ወደ መሬት በማውረድ በአማራ ክልል አዊ ዞን ከአኬሽያ ዲከረንስ ከሰል በሚከሰልበት ወቅት የሚለቀቀውን ከፍተኛ የሆነ የበካይ ጋዝ/ካርቦን ሞኖክሳይድ/ ልቀት ለማስቀረት ከቴክኖሎጂው የፈጠራ ባለቤት ጋር በጋራ የመስክ ምልከታ ተደርጓል፤ በመሆኑም ችግሩንም ለመፍታት የሚያስችል የቴክኖሎጂ አቅርቦት እንዳለ ከቴክኖሎጂው የፈጠራ ባለቤት ለመረዳት ተችሏል፡፡
- ከክሳይሜት ቴክኖሎጅ ሴንተርና ኔትወርክ /CTCN/ የሚገኘውን ሀገራዊ የቴክኒክ ድጋፍ አፈጻጸም አንድ ጊዜ ለመከታተልና ለመደገፍ ታቅዶ በጆኦተርማል የቀጥታ አጠቃቀም የአዋጭነት ጥናት (Geothermal Direct application prefeasibility project) የአፈጻጸም ደረጃ አንድ ጊዜ ተከናውኗል። ፕሮጀክቱ በተተገበረባቸው ፓይለት ቦታዎች አዋጭ የአረንጓዴ ቴክኖሎጂዎች ተለይተዋል። በቀጣይ ከ GCF በጀት ለማግኘት የሚያስችል መነሻ የጥናት ሰነድ ተዘጋጅቷል፡፡
- በአገር አቀፍ ደረጃ የአረንጓዴ ቴክኖሎጂዎችን ልማትና ሽግግር አፈጻጸም በተመለከተ መረጃዎችን የማሰባሰብ፣ የማጠናቀርና የማደራጀት ስራዎች ተከናውነዋል፡፡ በዚሁም መሰረት የቴክኖሎጅዎችን አፈጻጸም የሚያሳይ አንድ ሰነድ ተዘጋጅቶ ለ NDC highlight ለህትመት ተልኳል፡፡

**ዋና ተግባር 4 :- የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀት መቀነሱን ማረጋገጥ**

**የቁልፍ ውጤቶች አፈፃፀም:-**

- የመጀመሪያውን ሀገራዊ "Biennial Update Report (BUR) እና የ"Oromiya እና Dire Dewa GHG inventory" ዘገባ ዝግጅትን በሚመለከት:-
    - በአማካሪ ድርጅቶች የቀረበውን ፕሮግረስ ሪፖርት አጋር አካላት በተገኙበት ያለበትን ደረጃ ለማስገምገም ተችሏል፡፡ በግምገማውም ስራው ያለበትን ደረጃ ለመገምገም የተቻለ እና ግብአቶች የተገኙበት መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ በስራው ዙሪያ ያለውን ክፍተት ለሚሰራው አማካሪ ድርጅት በደብዳቤ እንዲያውቀው በማድረግ ሥራው በተያዘለት ጊዜ እንዲጠናቀቅ ክትትልና ድጋፍ እየተደረገ ነው፡፡
- ሀገራዊ የሦስተኛው National communication Report ዝግጅትን ለማሰራት ግልፅ ጨረታ በማውጣት አማካሪ ድርጅት እንዲቀጠር ተደርጎ የinception report እየተሰራ ይገኛል፡፡

- ከደን ዘርፉ የሚመነጨውን የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት ቅነሳ ሪፖርት ከአውሮፓ ህብረት ጋር በተፈራረምነው መሰረት አመሳካቱን ለማሳካት ከደን ዘርፍ 6 የMRV ባለሙያዎች፣ ከNational MRV ሦስት ባለሙያዎች እና ከጂኦስፓሻል ኢኒስቲትዩት አንድ ጂአይ ኤስ ባለሙያ ተመድቦ ስራው እየተሰራ ይገኛል፡፡
- የተከለሰውን በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ እቅድ (Updated NDC) የ10 ዓመት (2020-2030) የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት ቅነሳ ዕቅድ ለሚመለከታቸው የዘርፍ መ/ቤቶች በ10 ዓመት ዕቅዳቸው ውስጥ እንዲያካትቱ በደብዳቤ ተልኳል፡፡
- የአውሮፓ ህብረት በቀጣይ ድጋፍ ለማድረግ እንደ ሀገር ክፍተቶችን ለመለየት (Analysis and pre-identification of an EU “Framework Support Programme to Ethiopia” in the Green Deal Sector) የሚያስችል አንድ ኮሚቴ ተቋቁሞ ከሚመለከታቸው የአውሮፓ ህብረት ተወካዮች ጋር በመገናኘት ውይይት በማድረግ ግብዓት ተሰጥቷል፡፡
- በኢነርጂ እና በwaste ዙሪያ የሚለቀቀውን የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት ልኬት ለመስራት የአውሮፓ ህብረት አለማቀፍ የቴክኒክ አማካሪ (international Technical Assistance (TA)) ቀጥሮ የሚሰሩ ዝርዝር ስራዎች ዕቅድ ተዘጋጅቶ ከውሃ መስኖና ኢነርጅ ሚ/ር እና ከከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚ/ር የተመደቡ ሁለት ሁለት ባለሙያዎች ባሉበት በታቀደው ዕቅድ ዙሪያ ውይይት ተደርጎ ስራው እየተሰራ ይገኛል፡፡
- የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት ቅነሳ የልኬትና የዘገባ ጥራት ማረጋገጫና ቁጥጥርን ለማስጠበቅ የሚያስችል ስርዓትን በአማካሪ ለማስጠናት ከአማካሪው ድርጅት ጋር ኮንትራት ስምምነት ተገብቶ የሥራውን ሂደት የሚዘግብ (Inception Report) ቀርቦ ተተችቶ ስራው በዛው መሰረት ተሰርቶ የመነሻ ሰነድ (draft report) ተሰርቶ ቀርቦ የማስተቸት ስራ እየተሰራ ነው፡፡ ለስራው የሚያስፈልገው የ30% ቅድመ ክፍያ እንዲከፈላቸው ተደርጓል፡፡

**ዋና ተግባር 4 ፡- በዓለም አቀፍ የአካባቢ ስምምነቶች ድርድር መድረኮች እና ፎረሞች ላይ የሀገራችን ፍላጎትና አቋም የሚያሳዩ ሰነዶች ለማዘጋጀት**

**የቁልፍ ውጤቶች አፈፃፀም፡-**

በዓለም አቀፍ የአካባቢ ስምምነቶች ድርድር መድረኮች እና ፎረሞች ላይ የሀገራችን ፍላጎትና አቋም የሚያሳዩ 3 ሰነዶች ለማዘጋጀት ታቅዶ 6 ሰነዶች ተዘጋጅተዋል፡፡

- 76ኛዉን የተባሩት መንግስታት ጠቅላላ ጉባዔ (UNGA76) አስመልክቶ አንድ ሰነድ ማዘጋጀት በአየር ንብረት ለዉጥ ሳይ እንደ ሀገር የተሰሩ ስራዎች፣ ያጋጠሙ ችግሮች እና በቀጣይ የሚያስፈልጉ ድጋፎችን ያካተተ አንድ ሰነድ ተዘጋጅቷል፡፡
- በCOP26 ጉዳዮች ዙሪያ የሀገራችን ፍላጎትና አቋም የሚያሳይ አንድ ሰነድ ተዘጋጅቷል፡፡
- በዩናይትድ ኪንግደም በCOP26 ጉዳዮች ዙሪያ ስተዘጋጀው የአካባቢ ሚኒስቴሮች ስብሰባ የሚሆን የሀገራችንን ፍላጎትና አቋም የሚገልጽ አንድ ሰነድ ተዘጋጅቷል፡፡
- Taiwan Energy Low Carbon Development forum እና Towards a Nature Positive Fututre ስብሰባዎች ሳይ በክብርት ፕሬስዳንት ሳህለ ወርቅ ዘዉዴ አማካይነት የንግግር ሁለት ሰነዶች በማዘጋጀት ተልኳል፡፡
- ለ8ኛው የአፍሪካ የአካባቢ ሚንስትሮች ጉባኤ የሚሆኑ የሀገራችንን ፍላጎትና አቋም የሚገልጽ አንድ ሰነድ ተዘጋጅቷል፡፡
- በአካካቢ ዘርፍ በIllegal Trading of chemicals and hazardous waste ጉዳይ ሳይ እየተዘጋጀ በሚገኘው ሰነድ  ሳይ በአባልነት በመሳፍ ድጋፍ ተደርጓል፡፡

**ዋና ተግባር 4 :- በ 3 የአካባቢ ስምምነቶች ድርድር መድረኮች ተሳትፎ ማድረግ**

**የቁልፍ ውጤቶች አፈፃፀም:-**

በ 3 የአካባቢ ስምምነቶች ድርድር መድረኮች ተሳትፎ ስማድረግ ታቅዶ በ3 መድረኮች ሳይ ተሳፎ ተደርጓል፡፡

- እ.ኤ.አ ከጁሳይ 25-27/2021 በCOP26 ፕሬዝዳንት በሆነችው ዩናይትድ ኪንግደም አዘጋጅነት በCOP26 ጉዳዮች ዙሪያ በተደረገዉ የአካባቢ ሚኒስቴሮች ስብሰባ የLDC ቡድንን ጭምር በመወከል ተሳትፎ ተደርጓል፤ የተሳትፎ ሪፖርትም ተዘጋጅቶ ስሚመለከታው አካላት ተልኳል፡፡
- እ.አ.አ. ከሴፕቴምበር 13 እስከ 14/2021 እና ሴፕቴምበር 16 በተካሄደው በ8ኛው የአፍሪካ የአካባቢ ሚንስትሮች ጉባኤ ተሳፎ በማድረግ የሀገራችንን ፍላጎት በማንጸባረቅ በተዘጋጀው የውሳኔ ሰነድሳይ እንዲካተት ተደርጓል፡፡
- በአነስተኛ የእድገት ደረጃ የሚገኙ ሀገራት ቡድን እና የአየር ንረት ስውጥ ተጋላጭ ሀገራት ፎረም በ26ኛው የአየር ንብረት ስውጥ ጉባኤ ዙሪያ በተዘጋጁ የበላይ አመራሮችና የልዑካን

ቡድን መሪዎች ጨምሮ የባለሙያዎች ስብሰባዎች ላይ ተሳትፎ በማድረግ የሀገራችን ፍጎት የቡድኑ አቋም እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡

**በተጨማሪም ለCOP26 የሚያስፈልጉ ጉዳዮች ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ተሳትፎ ለማስተባበር በታቀደው መሰረት፡-**

- COP26 አስመልክቶ ተሳታፊዎች ተሳፊዎች ልየታና ምዝገባ፣ ስፖንሰር ማፈላለግ (ከተጠየቁ 15 የሚሆኑ ድርጅቶች ውስጥ EU እና WFP 5 ሰዎችን ድጋፍ አድርገዋል) ፣ የቪዛና የኮቪድ ክትባት (የተ.መ. ድጋፍ አድርጓል) በሚመለከት የማስተባበር ስራ የተሰራ ሲሆን በሩብ ዓመቱ ሁሉም እንደሚሳፉ የሚጠበቁ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች አስፈላጊውን ቅድመ ዝግጅት እንዲያካሄዱ ተደርጓል፡ ፡
- በድርድር መድረኩ አጀንዳዎች ምደባ በማካሄድ ከቡድኑ ጋር ሁለት ጊዜ ምክክር ተደርጓል፡፡

**ዋና ተግባር 5፡- ከልማት አጋር አካላት ጋር የአጋርነት መፍጠሪያና ማጠናከሪያ የሁለትዮሽና የባለብዙ 5 የውይይት መድረኮች ለማካሄድ**

**የቁልፍ ውጤቶች አፈፃፀም**

ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት የአካባቢ ስምምነቶች አጋርነት መፍጠርያና ማጠናከርያ የሁለትዮሽና የባለብዙ 5 የውይይት መድረኮች ለማካሄድ ታቅዶ 8 የውይይት መድረኮችና የድጋፍ መስጫ መድረኮች ተካሂደዋል፡፡ እነርሱም የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ሦስት የP4G እና CRGE Forum ሥራን የማስተባበር እና የክትትልና ድጋፍ ሥራ የተሰራ ሲሆን ዝርዝሩ ቀጥሎ ቀርቧል፡-
  - የP4G Call for partnership የተለያዩ አመልካቾች በኢትዮጵያ በኩል ኮንሴፕት ኖት እንዲያዘጋጁ አንድ ዎርክሾፕ በማዘጋጀት እና በቢሮ ደረጃ አስፈላጊዉ ሙያዊ ክትትልና ድጋፍ የተደረገ ሲሆን በኢትዮጵያ ለመስራት ካመለከቱ 16 የሚሆኑ አጋርነቶች ውስጥ አራቱ የመጨረሻ ግምገማውን ደርሰዋል፡፡
  - በP4G ስር የሚገኙ ሁለት አጋርነቶችን ክትትልና ድጋፍ ማድረግ Ethiopian Beverage Alliance for Water(EBAW) እና Agroforestry for People, Peace & Prosperity አጋርነቶች ጋር ተደጋጋሚ ውይይት በማድረግ ድጋፍ የተደረገ ሲሆን የመስክ ጉብኝትም

ተደርጓል፡፡ Sustainable food partnership/SFP በሚመለከት አንድ ጊዜ የባለ ድርሻ አካላት የምክክር መድረክ ላይ በማሳተፍ ድጋፍና ክትትል የተደረገ ሲሆን ኮሚሽን መ/ቤታችንን ጨምሮ ሌሎች ባድርሻ አካላት በትብብር መስራ የሚያስችሳቸውን የመግባቢያ ሰነድ ተፈራርመዋ፡ ፡ Geo Futures Investment — Geothermal energy በሚመለከት አንድ ስብሰባ በመሳተፍ ድጋፍ ተደርጓል፡፡

- የCRGE Forum ከምክትል ሊቀመንበሮች ጋር ምክክር በማድረግ የበላይ ኃላፊዎች ዓመታዊ የምክክር መድረክ ከኮፕ 26 በኃላ ለማዘጋጀት ስምምነት ተደርሶ እየተሰራ ይገኛል፡፡

➢ አምስት የሁለትዮሽ የውይይት መድረክ በማካሄድ አጋርነት ከመፍጠር/ከማጠናከር አንጻር፡-

- ከተባበሩት አረብ ኢምሬቶች እና ከእንግሊዝ ጋር በአየር ንብረት ለውጥ ጉዳዮች ዙሪያ በትብብር ለመስራት የሚያስችል ሁለት ውይይት ተደርጓል፡፡
- LeadIT በተመለከተ ኢንዱስትሪዎች ከአካባቢ ጋር የተጣጣመ አሰራር እንዲኖራዉ በፎረሙ ጽ/ቤት አማካኝነት ፍኖተ ካርታ ለማዘጋጀት ቅድመ ዝግጅት እየጠደረገ የሚገኝ ሲሆን ከፎረሙ ጽ/ቤት እንዲሁም ከንግድ እና ኢንዱስትሪ ሚንስቴር ጋር አንድ ጊዜ ዉይይት ተደርጓል፡፡
- በአውሮፓ የ(Green DEAL) ለኢትዮጵያ ድጋፍ ለማድረግ ባዘጋጀው ስብሰባ በመሳተፍ አስፈሳጊው አስተያየት ተሰጥቷል፡፡
- በ.ተ.መ.ድ የአየር ንብረት ለውጥ ስምምነት በኩል ለማጣጣሚያ ሲሰጥ ለታሰበው ድጋፍ (UN4NAP) በሚመለከት አንድ ስብሰባ በመሳተፍ ድጋፍ ሲሰጥ በሚገባቸው ጉዳዮች ሳይ መግባባት ተደርሷል፡፡
- በሀብት ማፈሳለግ የስራ ክፍል በተዘጋጀው resorce mobilization road map ሳይ አስተያየት ተሰጥቷል፡፡

**ግብ 5፡- የአካባቢ ህግ ተከባሪነት ማጎልበት**

**ዋና ተግባር 1 የአገልግሎት መስጫ ተቋማት ላይ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ**

**የቁልፍ ውጤቶች አፈፃፀም፡-**

- በስድስት አገልግሎት ሰጭ ተቋማት ላይ የክትትል እና ቁጥጥር ስራን ለመስራት ታቅዶ በስድስቱም አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ላይ የክትትል እና ቁጥጥር ስራ የተሰራ ሲሆን በሶስቱ አግልግሎት ሰጪ ተቋማት (ፒራሚድ ሪዞርት፤ አዱሳሳ ሪዞርት እና ባቡጋያ ሪዞርት) በ2013 ዓ.ም ክትትል ተደርጎ ደካማ የአካባቢ አያያዝ የነበራቸዉ እና ማስጠንቀቂያ የተሰጣቸዉ ሲሆኑ ሶስቱ ተቋማት ማለትም ሃይሌ ሪዞርት፣ ጀ ሪዞረት እና አዳማ አጠቃሳይ ሆስፒታል ለመጀመሪያ ጊዜ የታዩ ተቋማት ናቸዉ፡፡

በአብዛኛወቹ ክትትል የተደረገባቸዉ ሪዞርቶች የደረቅ ቆሻሻ እና የፍሳሽ ቆሻሻ ልየታና ቅነሳ ሳይንሳዊ የሆኑ የአያያዝ እና የአስተዳደር ከዚህ በፊት ያልነበራቸዉ ሲሆን በተሰጠታቸዉ ግብረ መልስ መሰረት አዱሳሳ ሪዞርት እና ፒራሚድ ሪዞረት የነበረዉን ችግር አስተካለዉ የተሻለ የቆሻሻ አያያዝ ስርአት ዘርግተዋል፡፡ በዚህም መሰረት በፊት በተሰጠዉ ግብረ መልስ ፒራሚድ ሪዞርት አዲስ የፍሳሽ ቆሻሻ ቴክኖሎጅ በማስገንባት የሆቴሉን ፍሳሽ በማጣራት ለተፈጥሮ ማደበሪያነት እና ዉሃዉን ለአትክልት በመጠቀም ጥሩ ተሞክሮ እንዳመጣ ለማየት ተችሏል፤ በተመሳሳይ አዱሳሳ ሪዞርት ከሀይቁ በጣም በቅርብ ርቀት የሚገኘዉን (Septic Tank) በማስቆም ሌሳ ትልቅ (Septic Tank) በፈር ዞንን (bufferzone) ጠብቆ በመገንባት ከዚህ በፊት ወደ ዉጭ ይፈስ የነበረዉን ፍሳሽ በማስቆም ማስተካካያ መስራታቸዉን ለማወቅ ተችሏል፡፡ነገር ግን ባቡጋያ ሪዞርት እና ጀ ሪዞርት አሁንም ቢሆን የፍሳሽ እና የደረቅ ቆሻሻ አወጋገዳቸዉ በጣም ችግር ያለበት ሲሆን በተለይም ባቡጋያ ሪዞርት ከዚህ በፊት በተሰጠው ግብረ-መልስ መሰረት የማስተካከያ እርምጃ ባለመውሰዱ አሁንም ለሀይቆቹ ስጋት እንደሆነ ቀጥሏል፡፡ ሃይሌ ሪዞርት ደረቅ ቆሻሻን በመለየት ህጋዊ በሆኑ አካላት እንዲወገዱ በማድረግ የተሻለ ስራ እየሰራ እንደሆነ ለማየት ተችሏል፡፡ ከዚህም ሌሳ በክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች በ1,850 በአገልግሎት መስጫ ተቋማት ሳይ ክትትልና ቁጥጥር ተደርጓል፡፡

ዋና ተግባር 2 በማምረቻ ተቋማት ሳይ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ

የቁልፍ ውጤቶች አፈፃፀም

- በአምስት የማምረቻ ተቋማት ሳይ ክትትል እና ቁጥጥር ለማድረግ ታቅዶ በኦሮሚያ ክልል ሶስት (አቢሲንያ ብረታ ብረት ፋብሪካ ፣ሀበሻ steel mills plc እና አዳማ ቆርቆሮ ፋብሪካ) እንዲሁም በሲዳማ ክልል ሁለት በድምሩ አምስት የማምረቻ ተቋማት ሳይ ቁጥጥርና ክትትል ስራ ተሰርቷል፡፡ በዚህም ለአቢሲንያ ብረታብረት ፋብሪካ እና ሀበሻ steel mills plc ፋብሪካዎች የመጨረሻ ማስጠንቀቅያ ለመስጠት ዘገባው እየተጠናቀረ ይገኛል፡፡ እንዲሁም በአዳማ ቆርቆሮ ፋብሪካ ፣ ቢ ጂ አይ ቢራ ፋብሪካ እና የሀዋሳ ሚሊንየም ፔፕስ ፋብሪካዎች ሳይ ግብ-ረመልስ ለመስጠት በሂደት ሳይ ነው፡፡ በተጨማሪም በክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች 3,479 በማምረቻ ተቋማት የክትትልና ቁጥጥር ሥራዎች ተሰርተዋል፡፡

ዋና ተግባር 3 በልማት ፕሮጀክቶች ላይ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ

የቁልፍ ውጤቶች አፈፃፀም

- በፌደራል ደረጃ ፈቃድ በወሰዱ ሶስት ግዙፍ የልማት ፕሮጀክቶች ላይ የክትትልና ቁጥጥር ሥራ ስማከናወን አቅዶ በሶማሌ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ውስጥ በሚገኙ ሶስት የመንገድ ፕሮጀክቶች ማለትም ባቢሌ -ፌቅ ሎት III የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክቶች፣ ፌቅ -ሀመሮ የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክቶች እና ጅግጅጋ - ገለልሽ - ደገግ ሎት II ፕሮጀክቶች ላይ የክትትልና ቁጥጥር ሥራን ተከናውኗል፡፡
- በተደረገው የክትትልና ቁጥጥር ሥራ ሶስቱም ፕሮጀክቶች የአካባቢው ማህበረሰብ ያለበትን የውሃ ችግር ስመቀነስ በተለያዩ ቦታዎች ኩሬ በማዘጋጀት ለእንስሳት ውሀ እንዲያገኙ እያደረጉ ሲሆን በተለይ ባቢሌ -ፌቅ ሎት III የጉድጓድ ውሃ በመቆፈር እና ለእንስሳት ውሃ መጠጫ ገንዳ በኮንክሪት በመገንባት አገልግሎት እየሰጠ እንደሆነ ለማየት ተችሏል፡፡ እነዚህ ፕሮጀክቶች ከአዘጋጇቸው የኩሬ ውሃ ለግንባታው አገልግሎት መጠቀማቸው ከማህበረሰቡ ጋር የውሃ ሽሚያ እንዳይኖር የጎላ ጠቀሜታ አለው፡፡ የተለያዩ የግብዓት ማምረቻ ቦታዎችን (የተመረጠ አፈር ፣የጠጠር፣ የድንጋይ ማምረቻና ያልተፈለገ አፈር መድፊያ የመሣሰሉ) ቦታዎችን ከሚመለከተው አካል ህጋዊ በሆነ መልኩ ተረክበው የሚጠቀሙ ሲሆን አፈጻጸማቸው በተለያዩ ደረጃ ቢለያይም ከመንገድ ሥራው ጎን ለጎን በተጠቀሙባቸው ቦታዎች ላይ የመልሶ ማልማት ሥራ እየሠሩ ይገኛሉ፡፡ በሌላ በኩል በክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች በ950 ልማት ፕሮጀክቶች ላይ የክትትልና ቁጥጥር ሥራዎች ተሰርተዋል፡፡

## ዋና ተግባር 4 በከተሞች ላይ የደረቅ ቆሻሻ ክትትል ማድረግ

**የቁልፍ ውጤቶች አፈፃፀም**

- በዚህ ሩብ አመት በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በሚገኙ ከተሞች ማለትም አዳማ፣ ቢሾፍቱ እና አሰላ ከተማ አስተዳደሮች ላይ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ክትትልና ቁጥጥር ተደርጓል፡ ፡በዚህም መሰረት ከተሞች የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ እቅድ ያዘጋጁ መሆኑን፣ ለዘርፉ የሀብት ምደባ መደረጉን፣ ለወጣቶች በዘርፉ የስራ ዕድል መፈጠሩን፣ የአደረጃጀት እና የሰው ሀይል ስምሪት ማሻሻያ የጀመሩ ከተሞች መኖራቸውን በጥንካሬ የተለዩ ሲሆን ነገር ግን ከተሞች በከተማው የሚመነጨውን ደረቅ ቆሻሻ ሙሉ ለሙሉ አሰባሰብ፣ ደረቅ ቆሻሻን ከምንጩ ጀምሮ ለመቀነስ ስራዎች አለመጀመራቸው፣ ቆሻሻን መለየትና ድጋሚ ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግና የቆሻሻ ቦታዎችን ኦዲት በማድረግ አወጋገዱ ጉዳት እንዳያስከትል በማድረግ ረገድ ጉድለቶች ታይተዋል፡፡

ለከተማ አስተዳደሮቹ ግብረመልስ ተሰጥቶ ለተግባረዊነቱ ክትትል እየተደረገ ይገኛል፡፡ በሴሳ በኩል በክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች በ68 ከተሞች ላይ ክትትልና ቁጥጥር ተደርጓል፡፡

**ዋና ተግባር 5 አካባቢያዊ ተቀባይነት ባለው መንገድ የተወገደ አደገኛ ቆሻሻ በቶን**

**የቁልፍ ውጤቶች አፈፃፀም**

- በ1ኛ ሩብ አመት 100 ቶን የዲቲቲ ኬሚካልን የማሸግና ከሀገር ውጪ አጓጉዞ የማስወገድ ስራ የታቀደ ሲሆን 140 ቶን የዲዲቲ ኬሚካልን ለማስወገድ የሚያስችል የመልሶ ማሸግ ስራ ተከናውኗል፡ ፡

**ዋና ተግባር 6 የይሁንታ ፈቃድ ያገኙና ተግባራዊ ያደረጉ የልማት ፕሮጀክቶች**

የቁልፍ ውጤቶች አፈፃፀም

- በፌዴራል ደረጃ ፈቃድ የሚሰጣቸው ወይም በባህሪያቸው ክልል ተሻጋሪ ተጽእኖ ሊያስከትሉ የሚችሉ *25* የተለያዩ ዘርፍ ፕሮጀክቶች የአካባቢያዊና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ሰነዶቻቸውን በመገምገም የይሁንታ ፈቃድ ሲያገኙ ብቻ ወደ ትግበራ እንድገቡ ለማድረግ ታቅዶ በዚህ የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ውስጥ ለ24 ፕሮጀክቶች ለግምገማ ቀርቧል፡፡ ከቀረቡት ፕሮጀክቶች ውስጥ ለ20ዎቹ የይሁንታ ፈቃድ የተሰጣቸው ሲሆን ቀሪው አራት ፕሮጀክቶች በግምገማ ላይ ይገኛሉ፡፡
- በፌዴራል ደረጃ የይሁንታ ፈቃድ የተሰጣቸው አምስት (5) ሜጋ ፕሮጀክቶች ላይ የአካባቢ ክዋኔ ኦዲት ለማድረግ ታቅዶ በመጀመሪያ ሩብ ዓመት በሶስት (3) ፕሮጀክቶች ላይ በገቡት ቃል እና በአካባቢና ማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ውስጥ በተቀመጠው የአካባቢ አያያዝ ዕቅድ መሰረት ወደ ትግበራ መግባታቸውን ለማረጋገጥ የአካባቢ ክዋኔ ኦዲት ተደርጎ ለአልሚዎቹ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስዱ ግብረ መልስ ተሰጥቷል፡፡

ዋና ተግባር 7 በአካባቢ ዘርፈ የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ

የቁልፍ ውጤቶች አፈፃፀም

- በአካባቢ ዘርፍ በአማካሪነት ለመሰማራት ጥያቄ ለሚያቀርቡ 175 ባለሙያዎችና ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለመስጠት ታቅዶ ለ261 ባለሙያዎችና ለ22 ድርጅቶች በድምሩ 283 ፈቃድ ተሰጥቷል፡፡ የተለያዩ የግብርና ምርቶችን ወደ ውጪ አገር ለሚልኩ ባለሐብቶች፣ ከልውጠ ህያው /Genetically Modified Organisms/ ነፃ መሆናቸውን በማረጋገጥ 150 ፈቃዶችን ለመስጠት ታቅዶ 287 ፈቃድ ተሰጥቷል፡፡

ዋና ተግባር 7. **በደን ዘርፍ የህብረተሰብ ግንዛቤ መፍጠር**

- በሩብ ዓመቱ በደን ልማትና እንክብካቤ ዙሪያ የማህበረሰቡን ግንዛቤ ከማስፋት አንጻር ለ12,500 የማህበረሰብ ክፍሎች ግንዛቤ ለመስጠት ታቅዶ በአንድ ክልል (በኦሮሚያ ክልል) ብቻ ለ125 786 (ሴ 29285) የማህበረሰብ ክፍሎች የግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ በመስራት ከዕቅድ በላይ ማከናወን ተችሏል፡፡

**ዋና ተግባር 8. በደን ላይ የሚደርሰውን ህገ ወጥ ተግባራትን መከላከልና መቆጣጠር**

- በሩብ ዓመቱ በደቡብ ክልል የደን ውጤቶችን ህጋዊ የይለፍ ፈቃድ ሳይኖራቸው 12.5 ኩ/ል ከሰል በህገወጥ መንገድ ሲዘዋወር ተይዞ እንዲወረስ ተደርጓል፡፡ በተመሳሳይ የደን ውጤቶችን በማዘዋወር በተሰማሩ 35 ግለሰቦች ላይ ህጋዊ እርምጃ በመውሰድ ጉዳያቸው በክስ አግባብ ተይዞ ይገኛል፡፡ እንዲሁም በህገ ወጥ ከተወረሱት የደን ምርቶችና ከቅጣት 350,000 /ሶስት መቶ ሃምሳ ሺህ ብር ገቢ ማግኘት ተችሏል፡፡

**ግብ 6 ፡- አገራዊ የደንና የጥበቃ ቦታዎች ሽፋንን ማሳደግ**

ዋና ተግባር 1 **ደን ልማት ማካሄድ**

**የቁልፍ ውጤቶች አፈፃፀም**

- የሀገራችንን የደን ሽፋን ለማሳደግ ከማድረግ አንፃር 0.8 ሚልዮን ሄ/ር የተከላ መሬት በመለየትና ደረጃቸውን የጠበቁ 4 ቢልዮን ችግኞች እንዲፈሉና እንዲተከሉ ለማድረግ ታቅዶ በክልሎችና በከተማ አስተዳደሮች በተደረገው የመስክ ክትትልና ድጋፍ **3.26 ቢሊዮን** የደን ችግኞች **በ** 699,281.05 **ሄ/ር** ላይ ተከላ ማካሄድ ተችሏል፡፡ ከተተከለው ችግኝ ውስጥ **በ67,578.9** ሄ/ር ላይ የተተከለው **42,111,161** የቀርከሀ ችግኝ ነው፡፡
- በተከላ ላይ የፕሮጄክቶች ተሳትፎ በተመለከተ በደን ሴክተር አቅም ግምባታ ፕሮግራም 19,968.19 ሄ/ር (በRIP 18,513.94 ሄ/ር፣ በCFSDP 907.25 ሄ/ር እና በIS-FSDP 547 ሄ/ር)፣ በአዳፕቴሽን ፈንድ ፕሮጀክት 57.68 ሄ/ር፣ በደን ሴክተር ትራንስፎርሜሽን ዩኒት 1684 ሄ/ር፣ በKFW ደን ልማትና ብዝሃ ሕይወት እንክብካቤ ፕሮጄክት 770 ሄ/ር እና CRFL (የDANIDA ድጋፍ) ፕሮጄክት 545.4 ሄ/ር፤ በአውሮፓ ህብረት በሚደገፍ ፕሮጅክት 2,455.56 ሄ/ር፣ በ Integrated landscape for Livelihood and Ecosystem 4,984.86 ሄ/ር፣ በIntegrated Rural Development project in Arid pastoral areas 11 ሄ/ር በድምሩ 30,476.7 ሄ/ር ላይ መትከል ተችሏል፡፡

- በኮሚሽን መስሪያ ቤታችን እና በተጠሪ ተቋማት በየደረጃው ባሉ ሰራተኞች በአዲስ አበባ ከተማ እና በክልሎች በ1,145.45ሄ/ር ተከላ ስማካሄድ ታቅዶ በ1412.2 ሄ/ር ላይ 1,832,107 ችግኞችን ለመትከል ተችሏል፡፡

የክልሎችንና የከተማ አስተዳደሮችን አፈጻጸም በተመለከተ ቀጥሎ ባለው ሠንጠረዥ1 ቀርቧል፡፡

| ክልል | የተተከለ ችግኝ ቁጥር | በተከላ የተሸፈነ መሬት መጠን በሄ/ር | ምርመራ |
|---|---|---|---|
| ኦሮሚያ | 1,798,280,000 | 416,276.62 | |
| አማራ | 604,700,000.00 | 83,191.00 | |
| ደቡብ | 636,735,537.00 | 144,858.00 | |
| ሲዳማ | 185,541,435.00 | 40,621.81 | |
| ሶማሌ | 918,150.00 | 367.26 | |
| ቤኒሻንጉል ጉምዝ | 25,114,734.00 | 8,629.00 | |
| ጋምቤላ | 2,182,916.00 | 3,872.00 | |
| ሀረሪ | 145,898.00 | 58.36 | |
| ድሬደዋ | 811,677.00 | 757.00 | |
| አዲስ አበባ | 5,997,261.00 | 650 | |
| Total | 3,260,427,608.00 | 699,281.05 | |

- የ2020ና 2021 ሃገራዊ የደን ሽፈን መጠንን ለማስላት የሚያስችሉ 16,755 የሶፍትዌር ማለማመጃ ናሙናዎችን የሳታላይት ምስል በመጠቀም ለመሰብሰብ ታቅዶ 12,926 ወካይ ናሙናዎችን ለመሰብሰብ ተችሏል፡፡ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የልማትና ክርስታናዊ ተራድኦ ኮሚሽን (Ethiopian Orthodox Tewahedo Church Development and Inter-Church Aid Commission) ጋር በመቀናጀት የገዳማትና አብያተክርስቲያናት የሚገኝ የደን ማኔጅመንት እቅድ ለማዘጋጀት የሚረዱ ስራዎች በተመለከተ የ 6 ገዳማትና የ 3 ቤተክርስቲያን ደን ወሰን የማካለልና የጂፒኤስ መረጃ መሰብሠብ ተችሏል፡፡

ተግባር 2 ፡- የደን ጥበቃ ማካሄድ

የቁልፍ ውጤቶች አፈጻጸም፡-

- በሩብ ዓመቱ አገራዊ የደን ሽፋንን ከማሳደግ አንጻር 19.47 ሚ/ሄ/ር ነባር የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ደኖችን የመጠበቅ፣ የመንከባከብና በዘላቂነት እንዲጠበቅ ታቀዶ በተከታታይ በተደረገው የመስክ ክትትልና የሙያ ድጋፍ መሰረት 19.47 ሚ/ሄ/ (100%) የተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ ደን የመጠበቅና የመንከብከብ ስራ ተከናውኗል፡፡

**ግብ.9 - በ"አካባቢ እና በብዝሀ-ሕይወት ሀብት  ላይ ሊከሰት የሚችለውን ጉዳት መቀነስ**

**በቁልፍ የውጤት አመልካቾች (KPIs) ላይ የተመሰረተ የፊዚካል ዕቅድ አፈፃፀም ትንተና**

- ብሔራዊ የደህንነት ህይወት አማካሪ ኮሚቴ ስራን ለማስተባበር 1 ጊዜ ታቅዶ ማከናወን ተችሏል አፈጻጸሙ በመቶኛ ሲቀመጥ 100% ማድረስ ተችሏል፡፡
- በልውጠ ህያው ምርምር እና ሙከራ ጣቢያዎች ተገኝቶ በቀረበው የምርምር ፕሮቶኮል መሰረት ሙከራው መከናወኑን ለማረጋገጥ 1 ጊዜ ክትትልና ቁጥጥር ለማድረግ ታስቦ በሆለታ ኤና ጀልዱ የምርምር ሙከራ ጣቢያዎች የተከናወነ ሲሆን አፈፃፀሙም 100% ማድረስ ተችሏል፡፡
- ውጤታማነታቸውን የተረጋገጡ የምርምርና ቴክኖሎጂ ውጤቶችን በመጠቀም እና የአካባቢ ህ/ሰብንና ሌሎች ያገባናል የሚሉ አካላት  ያሳተፉ ሥራዎችን በመሥራት በሀገር ደረጃ አሁን ያለውን የ2 ሚሊዮን ሄክታር የወራሪ መጤ ዝሪያዎች ሽፋን 34ሺህ ሄክታር እንዲቀንስ በማድረግ አፈጻጸሙ በመቶኛ ሲቀመጥ 97.14% ነው፡፡
- በሩብ ዓመቱ ሀገራዊ የደን እሳት መከላከል ፖሊሲና ስትራቴጂ ማዘጋጀት እና በ0.035 ሚ/ሄ/ር በሬት ላይ የሚገኙ መጤና ወራሪ አረሞችን መቀነስ የሚሉ ተግባራት ተቅደው ፖሊሲና ስትራቴጂውን ከማዘጋጀት አንጻር የመረጃ ማሰባሰብ ስራ እየተሰራ ሲሆን በጤና ወራሪ አረሞችን ከመቀነስ አንጻር የታቀደውን አቅድ መከናወኑን ለማወቅ ከክልሎች ሪፖርት ባለመላኩ ምክንያት ክንውኑ ምህል ያህል እንደሆነ ለማወቅ አልተቻለም፡፡

**ግብ 10፡- የመረጃና ቴክኖሎጂ አቅርቦትና ሽግግርን ማሳደግ**

**የቁልፍ ውጤቶች አፈጻጸም፡-**

- በዘመናዊ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ በመጠቀም የዘርፉን የመረጃ አሰባሰብ፣ አያያዝና አጠቃቀም እና የልውውጥ ስርዓት ለማዘመን 1 ስረዓት ለመዘርጋ ታቅዶ አንድ የዛፍ ዘር ገበያ ትስስርና ክትትል መረጃ ስረዓት ተዘርግቷል፡፡

**ግብ 11 ፡- የወጣቶችና ሴቶች ተሳትፎና ተጠቃሚነት ማሳደግ**

**የቁልፍ ውጤቶች አፈጻጸም፡-**

- በሩብ ዓመት 0.025 ሚልዮን ለሚሆኑ ወጣቶችንና ሴቶች የስራ እድል ለመፍጠር ታቅዶ በአማራ 26,609 (ሴት 8,736)፣ በኦሮሚያ 6,693 (ሴት 2820)፤ በደቡብ 3634 (ሴት 1006)፤ በደን ኢንዱስድትሪዎች 657(ሴት 165)፣ በአዲስ አበባ 22 (ሴት 7)፣ በድሬደዋ 289(ሴት 145)፣ በጋምቤላ 100 (ሴት 60) እንዲሁም በሶማሌ 370 (ሴት 99) በድምሩም 38,374 (ሴት 13038) ለሚሆኑ ዜጎች በተለያዩ የዘርፉ ስራዎች ግዜያዊ እና ቋሚ ስራ በመፍጠር ከዕቀድ በላይ ማከናወን ተችሏል፡፡ ከዚህ ወስጥ በደን ሴክተር አቅም ግንባታ ፕሮግራም 2,238 (ሴት 836) ተጠቃሚ የሆኑ ሲሆን ከዚህ ዉስጥ 671 ወጣቶች (ወጣት ሴቶች 200) ናቸው፡፡
- **በ 1ኛ ሩብዓመት 62,500** ሴቶችንና ወጣቶችን በአካባቢ፣ ደንና አየር ንብረት ለውጥ ዘርፍ ስራ ዕድል በመፍጠር ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ ለ**7,773** ሴት እና ለ**12,958** ወንድ በድምሩ ለ**20,731** ሴቶችና ወጣቶች ስራ እድል ለመፍጠር ተችሏል፡፡

**ግብ.13፡-ዘርፉ ለአገራዊ የኢኮኖሚ እድገት የሚያበረክተውን ድርሻ ድርሻ ከ4 %በመቶ ወደ 8 % ማሳደግማሳደግ፣**

**የቁልፍ ውጤቶች አፈጻጸም፡-**

- በ2013 በጀት ዓመት በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በሀዊ ዞን አንገሻ ወረዳ ውስጥ የሚገኝ ጥርባ ሀይቅ እና በባንጃ ወረዳ ውስጥ የሚገኝ ዘንገና ሐይቅ የተጀመሩ የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት የሚያመነጩትን ዋጋ ትመና ጥናት ሪፖርት 50% ለማዘጋጀት ታቅዶ 50ም% የተከናወነ ሲሆን 100% ተከናውኗል፡፡
- በበጀት ዓመቱ በ2.12 ሚ/ን ሄ/ር መሬት ላይ የሚገኙ የተፈጥሮ ደኖችን በአሳታፊ የደን አስተዳደር ስርዓትን በመተግበር በዘላቂነት እንዲጠበቁና ተገቢውን ግልጋሎት እንዲሰጡ ለማድረግ ታቅዶ በዚሁ መሰረት በተለይ የተሻለ የአሳታፊ ደን አስተዳደር ስርዓት ከተገበሩት

ክልልች ማለትም ከኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስትና ከደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት በተደረገው የመስክ ክትትልና በሌሎች ክልሎች በተደረገው የስልክና የኢሜል የመረጃ ልውውጥ 2.12 ሚ/ሄ/ር የተፈጥሮ ደን በአሳታፊ የደን አስተዳደር ስርዓት እየተዳደረና ተገቢው ጥቅም እያስገኘ መሆኑን ከተሰበሰበው መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

- በሩብ ዓመቱ ለአገር ውስጥና ለውጭ ገበያ የደን ምርት ለማቅረብ የታቀደ ባይሆንም 303.7 ቶን የደን ምርት ውጤት(አጠና 232.9 ቶን ፈርኒቸር 70.8 ቶን )ወደ ውጭሀገር በመላክ 0.114 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር የውጭ ምንዛሬ (5.127606 ብር) ለማግኘት ተችሏል፡፡

**ግብ 14፡- የዘርፉን የመፈጸምና የማስፈጸም አቅም ማሳደግ**

የቁልፍ ውጤቶች አፈጻጸም፡-

- በዚህ ሩብ ዓመት ለ600 ፈጻሚና አስፈጻሚ አካላት ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ75181 ፈፃሚና አስፈፃሚ አካላት ስልጠና ተሰጠቷል፡፡
- ለአዲስ አበባ አካባቢ ጥበቃና አረንጓዴ ልማት ኮሚሽን መ/ቤት ተጠሪ ተቋማት የከተሞችን በሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት ቅነሳ አሰራርና ለስራው መጠቀም ያለባቸው software እና guideline ዙሪያ የበጀት ድጋፍ እና የአቅም ግንባታ ስልጠና ለ46 ባለሙያዎች (ሴ 9) ለተከታታይ 5 ቀናት ተሰጥቷል፡፡
- ከ WRI ጋር በጋራ በመሆን በሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት ልኬት፤ምዝገባና ማረጋገጫ ዙሪያ ለ12 የዘርፍ ሚ/መቤቶች እና ለኮሚሽን መ/ቤት ለ16 (ወንድ 14) ባለሙያዎች ስልጠና ለመስጠት ተችሏል፡፡

### ክፍል ሁለት

## 1. የተቋሙ የፋይናንስ/ፕሮግራም በጀት አፈፃፀም

### ሠንጠረዥ የ2014 በጀት ዓመት የ1ኛ ሩብ ዓመት የበጀት አፈጻጸም በየ ፕሮግራሙ

| ፕሮግራም | ዕቅድ | ክንውን | በመቶኛ |
|---|---|---|---|
| **ፕሮግራም 1፡-** የስራ አመራርና አስተዳደር | 46,662,293.00 | 27,512,285.36 | 58.96 |
| ፕሮግራም 2፡01፡- አካባቢ ህግ ተከባሪነት ማረጋገጥ | 8,746,472.00 | 2,503,780.48 | 28.63 |
| ፕሮግራም 2፡ 02፡- በአየር ንብረት ለውጥና ብዝሀ ህይወት ዘርፍ የሚተገበሩ ሥራዎች ን ማስተባበር | 32,069,775.00 | 869,722.74 | 2.71 |
| ፕሮግራም 2፡ 03፡- የተቀናጀ የመሬት አጠቃቀም ዕቅድና ፖሊሲ ማዘጋጀት | 9,919,418.00 | 645,460.56 | 6.51 |
| ፕሮግራም 3፡ 01፡- የተፈጠሮ ደን ልማት ጥበቃና እንክብካቤ ሥራዎችን ማስተባበርና መደገፍ | 103,768,944.00 | 956,649.22 | 0.92 |
| ፕሮግራም 3፡ 02፡- ሰው ሰራሽ ደን ልማትና እንክብካቤን ማጠናከር | 2,931,591.00 | 277,109.28 | 9.45 |
| ፕሮግራም3፡ 03፡- የደን አጠቃቀም ግብይት ማስፋፊያ ና ቁጥጥር ማካሄድ | 2,773,041.00 | 297,095.94 | 10.71 |
| ድምር | 206,871,534.00 | 33,062,103.58 | 15.98 |

### 3.1. የኦዲት ግኝት ምልከታ

- ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ስልት በጄነራል ኦዲተር በተሰጡ የአፈጻጸም የማስተካከያ ምክረ ሀሳቦች መሰረት አስፈላጊውን በመፈጸም ሪፖርት ተዘጋጅቷል፡ ፡

### 3.2. ለክልሎች የተሰጠ አቅም ግንባታ

- በተያዘዉ ሩብ አመት ለ5 ክልሎች እና ለ1 ከተማ አስተዳደር (ለሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፣ ለደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት፣ ለጋምቤላ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፤ ለቤንሻንጉል ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፣ ለኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስትና ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር) በተቀናጀ የአካባቢ ሁኔታና ለዉጥ ዘገባ ጥናት (Integrated Environmental Assessment (IEA) ላይ ለ 80 ሙያተኞች ስልጠና ለመስጠት የታቀደ ሲሆን ከ100 ፐርሰንት በላይ ማከናወን ተችሏል፡፡

- ክልሎች ክልላዊ የአካባቢ ሁኔታና ለውጥ ዘገባ ሪፖርት እንዲያዘጋጁ ለ3 ክልሎችና ለ1 ከተማ አስተዳደር (ለሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፤ለደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት፣ ሀረሪ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስትና ለድሬደዋ ከተማ አስተዳደር) የድጋፍና ክትትል ስራ ተደርጓል፡፡
- የሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የአካባቢ ጽ/ቤቶች በ26ኛው የተ.መ. የአየር ንብረት ለውጥ ጉባኤ እንዲሳተፉ ግብዣ ተደርጎላቸው ተሳፎዓቸው የተሳካ እንዲሆን የግንዛቤ ማስጨበጫ የተሰጠ ሲሆን ሌሎች የሎጅስቲክና ሙያዊ ድጋፍና ክትትል እየተደረገ ነው፡፡
- ለአዲስ አበባ አካባቢ ጥበቃና አረንጓዴ ልማት ኮሚሽን መ/ቤት ተጠሪ ተቋማት በሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት ቅነሳ ዙሪያ ባሉ አሰራሮች ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡
- በችግኝ ተከላ ወቅት በአመራርና በባለሙያ ደረጃ ከሚመለከታቸው አጋር አካላት ጋር በመቀናጀት የተጠናከረ የሙያና አስተዳደራዊ ድጋፍ እንዲሰጥ ተደርጓል፣
- በአዲስ አበባ በጉለሌ እፅዋት ማዕከል በባህር ዛፍ ላይ በተከሰተው በሽታ ዙሪያ ማዕከሉ ማድረግ ያለበትን ጥንቃቄ ዙሪያ ሙያዊ ድጋፍ ተሰጥቷል፣

ክፍል ሶስት

# 4. በአፈፃፀም ሂደት ያጋጠሙ ተግዳሮቶችና የተወሰዱ የመፍትሔ እርምጃዎች

## 4.1. ተግዳሮቶች

- ወደ ውጪ አገር የሚላኩ የተለያዩ የግብርና ምርቶችን ከልውጠ ህያው /Genetically Modified Organisms/ ነፃ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ የላቦራቶሪ ምርመራ አለመጀመር፡፡
- ከተለያዩ ባድርሻ አካላት በአካባቢ ስምምነቶች የድርድር ሂደት ያለው የመረጃ ልውውጥና በቅንጅት የመስራት ክፍተት ያለው ነው፡፡
- የህግ ማስከበር ክፍተት በመኖሩ ምክንት በደን ላይ እየደረሰ ያለው መጨፍጨፍ በመራከት፣

## 4.2. የተወሰዱ/ሲወሰዱ የሚገባቸው/ የመፍትሄ እርምጃዎች

- የለቦራቶሪ ምርመራ ለመጀመር ቅድመ ሁኔታዎች የተጠናቀቁ ሲሆን ስራዉ እስከሚጀመር ድረስ የግብርና ምርቶቹ ከላቸዉ የዉጪ ሚንዛሪ ፋይዳ አንፃር የአገር ዉስጥ ምርቶች መሆናቸዉን በማየት ፈቃድ መስጠት፡፡
- ከፎካል ፐርሰኖች ጋር በጎንዮሽ በመነጋገር የአካባቢ ስምምነቶች የድርድር ሂደት ያለበትን ደረጃ እና የዝግጅ እንዲሁም የተገኙ ውጤቶች መረጃ ለመውሰድ ተሞክሯል፡፡

## 5. ሠንጠረዥ በየዘርፉ ቁልፍ የውጤት መስኮችንና ቁልፍ የውጤት አመልካቾችን(የፖሊሲ ማትሪክሱን) መሰረት በማድረግ የሚዘጋጅ[1]

| ተ.ቁ | የአፈጻጸም አመልካቾች | | መለኪያ | መነሻ 2013 | የ2014 በጀት አመት ኢላማ | 1ኛ ሩብ ዓመት | | አፈጻጸም በ% |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | ዕቅድ | ክንውን | |
| | ግብ 2 :- የሀብት አጠቃቀም ዉጤታማነትን ማሳደግ | | | | | | | |
| | ጥቅም ላይ የዋለ በጀት | | በመቶኛ | | 100 | 100 | 100 | 100 |
| | በኦዲት ግኝት ላይ የተወሰደ ማስተካከያ እርምጃ | | በመቶኛ | | 100 | 25 | 25 | 100 |
| | የቀነሰ የሀብት ብክነት | | በመቶኛ | | 100 | 100 | 100 | 100% |
| | ግብ 3 :- የሀብት ግኝትን ማሳደግ | | | | | | | |
| | ከደን ሮያሊቲ የተገኘ | | በሚሊዮን ብር | 257.96 | 200 | 10 | 49.281 | ›100 |
| | ያደገ የቱሪስት ፍሰት | የውጭ ሀገር | በሺ ቁጥር | 53.34 | 100 | 10 | 7 | 70 |
| | | የሀገር ውስጥ | በሺ ቁጥር | | 60 | 10 | 6 | 60- |

| ተ.ቁ | የአፈጻጸም አመልካቾች | | መስኪያ | መነሻ 2013 | የ2014 በጀት አመት ኢላማ | 1ኛ ሩብ ዓመት | | አፈጻጸም በ% |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | ዕቅድ | ክንውን | |
| | ከሀገር ውስጥ እና ከውጭ ቱሪስት ጎብኚዎች የተገኘ ገቢ | | በሚሊዮን ብር | 36.29 | 170 | 10 | 6 | 60 |
| | **ግብ4 :- ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ትግበራን ውጤታማነት ማሻሻል** | | | | | | | |
| | ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ትግበራ | ሜይንስትሪሚንግ ያደረጉ ተቋማት | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100% |
| | | ለዘርፍ መ/ቤቶች የተሰጠ ግብረ መልስ | በቁጥር | 4 | 4 | 1 | 1 | 100% |
| | የሀገራችን ፍላጎትና አቋም የሚያሳዩ የተዘጋጁ ሰነዶች | | ቁጥር | 27 | 18 | 3 | 6 | >100% |
| | ተሳትፎ የተደረገባቸው የአካባቢ ስምምነቶች ድርድር መድረኮች | | ቁጥር | 16 | 18 | 3 | 3 | 100% |
| | የተዘጋጁና ተሳትፎ የተደረገባቸው የአጋርነት መፍጠሪያና ማጠናከሪያ የሁለትዮሽና የባለብዙ የውይይት መድረኮች | | ቁጥር | 50 | 50 | 5 | 8 | >100% |
| 2 | **ግብ 5 :- የአካባቢ ህግ ተከባሪነት ማጎልበት** | | | | | | | |
| | የተዘጋጁ የአካባቢ ህግ ስርዓቶች | | በቁጥር | 6 | 6 | - | 1 | >100% |
| | ግንዛቤ ያገኙ የህብረተሰብ አካለት በሚሊዮን ቁጥር | | በሚሊየን | 2.1 | 4 | 0.5 | 1.5 | 300% |

| ተ.ቁ | የአፈጻጸም አመልካቾች | መስኪያ | መነሻ 2013 | የ2014 በጀት አመት ኢላማ | 1ኛ ሩብ ዓመት | | አፈጻጸም በ% |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | ዕቅድ | ክንውን | |
| | የተቀናጀ ደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ዕቅድ አዘገጅተው እየተገበሩ ያሉ ከተሞች | ክትትልና ድጋፍ የተደረገ | 643 | 750 | 100 | 65 | 65 |
| | በአገሪቱ ስታንዳርድ መሰረት ቁጥጥር የተደረገባቸው ተቋማትና ፕሮጀክቶች ብዛት | በቁጥር | 13100 | 14412 | 3000 | 3479 | ›100% |
| | የአካባቢ አያያዝ ክትትል እና ቁጥጥር የተደረገባቸው ፕሮጀክቶች ብዛት | በቁጥር | 4359 | 5863 | 800 | 950 | ›100% |
| | የአካባቢ ብክለት ይወገድልኝ አቤቶታና ጥቆማ በመቀበል ማጣራትና ምላሽ መስጠት | በቁጥር | 2527 | 2696 | 300 | 215 | 71.66 |
| | የተለያዩ የዘርፍ ፕሮጀክቶች የአካባቢያዊና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ሰነዶቻቸውን በመገምገም የይሁንታ ፈቃድ ሲያገኙ ብቻ ወደ ትግበራ እንድገቡ ማድረግ፤ | በቁጥር | 7000 | 7300 | 1300 | 894 | 68.76 |
| | የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ሳያካሂዱ ወደ ሥራ የገቡ ነባር ፕሮጀክቶችን የአካባቢና ማህበረሰብ አያያዝ ዕቅድ እዲያቀርቡና እንዲያጸድቁ ማድረግ | በቁጥር | 1089 | 1520 | 100 | 606 | ›100% |

| ተ.ቁ | የአፈጻጸም አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ 2013 | የ2014 በጀት አመት ኢላማ | 1ኛ ሩብ ዓመት | | አፈጻጸም በ% |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | ዕቅድ | ክንውን | |
| | የይሁንታ ፈቃድ ለተሰጣቸው ፕሮጀክቶች እና ፓርኮች የአካባቢ ክዋኔ ኦዲት በማድረግ ክፍተት ባላቸው ፕሮጀክቶች ላይ የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ | በቁጥር | 400 | 5117 | 1000 | 1532 | ›100% |
| | በአካባቢ ዘርፍ የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ብዛት | በቁጥር | 447 | 1150 | 200 | 570 | ›100% |
| | አካባቢያዊ ተቀባይነት ባለው መንገድ የተወገደ አደገኛ ቆሻሻ | በቶን | 220 | 400 | 100 | 140 | ›100% |
| | ግብ 6 ፡- አገራዊ የደንና የጥበቃ ቦታዎች ሽፋንን ማሳደግ | | | | | | |
| | የዛፍ ዘር ማሰባሰብና ማሰራጨት | በቶን | 457.093 | 325 | - | 3 | ›100% |
| | የተጠበቀ ነባር፣ የተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ ደን | በሚ/ሄ/ር | 19.47 | 19.47 | 19.47 | 19.47 | 100% |
| | የዛፍ ተከላ የሚካሄድበት መሬት | በሚ/ሄ/ር | 0.772 | 0.8 | 0.8 | 0.699 | 87.4% |
| | ያገገመ የተራቆተ የደን መሬት | በሚ/ሄ/ር | 0.638 | 1 | - | - | - |
| | የቀርከሀ ደን ማልማት | በሚ//ሄ/ር | 0.015 | 0.02 | 0.02 | 0.0676 | ›100% |
| | በዱር እንስሳ ብ/ፓርኮች በ50 ሄክታር የተተከለ ሀገር በቀል ችግኝ በሺኛ | በቁጥር | 175.94 | 125 | 125 | 125 | 100 |
| | ግብ 9፡- በአካባቢ እና በብዝሐ-ህይወት ላይ ሊከሰት የሚችለውን ጉዳት መቀነስ | | | | | | |

| ተ.ቁ | የአፈጻጸም አመልካቾች | | መለኪያ | መነሻ 2013 | የ2014 በጀት አመት ኢላማ | 1ኛ ሩብ ዓመት | | አፈጻጸም በ% |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | ዕቅድ | ክንውን | |
| | የደን እሳት ተቆጣጣሪ ግብረ ሃይል ማጠናከር | | በቁጥር | 7 | 5 | - | 1 | 100% |
| | የቀነሰ መጤ ወራሪ አረም ሽፋን መጠን | | በሚ/ሄ/ር | 0.162 | 0.16 | 0.035 | 0.034 | 97.14 % |
| | ግብ 10:- የመረጃና ቴክኖሌጂ አቅርቦትና ሽግግርን ማሳደግ | | | | | | | |
| | የመረጃ አሰባሰብ፣ አያያዝና አጠቃቀም እና የልውውጥ ስርዓት ዕድገት | | በመቶኛ | 20 | 30 | - | 1 | 100% |
| | ስራ ላይ የዋለ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሥርዓት | | በቁጥር | 15 | 4 | 1 | 1 | 100% |
| | በአካባቢ ደንና አየር ንብረት ለውጥ ዙሪያ የወጡ የምርምር ውጤቶች | መረጃዎች | በቁጥር | 58 | 60 | 2 | 2 | 100% |
| | ግብ 11 :- የወጣቶችና ሴቶች ተሳትፎና ተጠቃሚነት ማሳደግ | | | | | | | |
| | የስራ ዕድል የተፈጠረላቸው ዜጎች በሚሊዮን ቁጥር | | በቁጥር | 0.349 | 0.5 | 0.125 | 0.059063 | 47.25 % |

| ተ.ቁ | የአፈጻጸም አመልካቾች | መስኪያ | መነሻ 2013 | የ2014 በጀት አመት ኢላማ | 1ኛ ሩብ ዓመት | | አፈጻጸም በ% |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | ዕቅድ | ክንውን | |
| | በደን ዘርፍ ከተፈጠረ የሥራ ዕድል ተጠቃሚ የሆኑ ወጣቶች ድርሻ በመቶኛ | በመቶኛ | 44 | 45 | 45 | 20689 | ›100% |
| | በደን ዘርፍ ከተፈጠረ የሥራ ዕድል የሥራ ዕድል ተጠቃሚ የሆኑ ሴቶች በሚሊዮን | በቁጥር | | 0.1125 | 0.011 25 | 0.01303 | 115.82 % |
| | በኮሚሽን መ/ቤቱ በሚገኙፕሮጀክቶች የሴቶችና ወጣቶችን ተጠቃሚነትን በመስክ ክትትል ማድረግ | በቁጥር | 5 | 4 | 1 | 1 | 100% |
| | ግብ 12 :- የዘርፉን የመሰረተ ልማት ሽፋን ማሳደግ | | | | | | |
| | የአካባቢና የደን ምርምር ላቦራቶሪ G+5 ግንባታ | በመቶኛ | | 30 | - | 1 | 100% |
| | የደን ዉጤቶች እናቬሽን ምርምር ላቦራቶሪ ኮምፕሌክስ G+3 ግንባታ | በመቶኛ | 13.96 | 50 | | 1 | 100% |
| | ግብ 13 :- ዘርፉ ለአገራዊ የኢኮኖሚ እድገት የሚያበረክተውን ድርሻ ከ4 በመቶ ወደ 8 በመቶ ማሳደግ | | | | | | |
| | የአሳታፊ የደን አስተዳደር ስርዓት ተግባራዊ የተደረገለት የተፈጥሮ ደን | ሚ/ሄ/ር | 2 | 2.12 | 2.12 | 2.12 | 100% |
| | በደን ዘርፍ የተሰማሩ ባለሀብቶች | በቁጥር | 100 | 100 | 10 | 88 | ›100% |

| ተ.ቁ | የአፈጻጸም አመልካቾች | | መለኪያ | መነሻ 2013 | የ2014 በጀት አመት ኢላማ | 1ኛ ሩብ ዓመት | | አፈጻጸም በ% |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | ዕቅድ | ክንውን | |
| | የስርዓተ ምህዳር ግልጋሎት ዋጋ ትመና የቅድመ ጥናት ማድረግ | | በቁጥር | 3 | 3 | 1 | 0 | 0 |
| | ሥርዓተ ምህዳሮች የሚያመነጩትን ሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ዋጋ መተመን፣ | | በቁጥር | 2 | 2 | 1 | 1 | 100% |
| | **ግብ 14:- የዘርፉን የመፈጸምና የማስፈጸም አቅም ማሳደግ** | | | | | | | |
| | የተሰጠ የአጭር ጊዜ ስልጠና | ወንድ | በቁጥር | | 2100 | - | 75181 | ›100% |
| | | ሴት | በቁጥር | | 900 | - | | |
| | የተሰጠ የረጅም ጊዜ ስልጠና በቁጥር | በመጀሪያ ድግሪ | በቁጥር | | 13 | | 15(2) | ›100% |
| | | በሁለተኛ ዲግሪ | በቁጥር | | 73 | | | |